Monthly Newsletter Vol 16 No.1



Page 5

## ICTD GIVES TRAINING

# ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY

JULY 2019

BUILDING CAPACITES IN THE PUBLIC SECTOR

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ

## የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የ2011 ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ግምገማ ቆጠራ

Page 6

## ECSU GRADUATES STUDENTS

Page 1





Page 4

## ECSU Council Evaluates the Annual Plan Performance

ECSU Est. 1995

## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY GRADUATES STUDENTS — 1

ECSU COUNCIL EVALUATES THE ANNUAL PLAN PERFORMANCE — 4

ICTD GIVES TRAINING — 5

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የ2011 ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ግምገማ ቅኝት — 6

ለኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ ፖሊሶች ስልጠና ተሰጠ — 11

2011 ዓ.ም የስራ ዘመን ማጠቃለያ ክብረ በዓል — 12



Editor In -Chife
Wondimu Moges

Editors
Wondimu Moges
Tariku Ayano
Anteneh Demisse

Photos
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

Graphics Design
Dereje Tesfaye

PRINTED BY
International & Public Relations Directorate



ECSU
International & Public Relations Directorate
Tel.0116462887
0116463015
E-mail;IPRD@ecsu.edu.et/
pr.ecsu@gmail.com
Po.box 5648
website;www.ecsu.edu.et
FM RADIO 100.5 MHz

# Ethiopian Civil Service University Graduates Students



Ethiopian Civil Service University graduated more than 1531 students with Bachelor, Masters and Doctoral Degrees on the 7th July 2019 in the presence of His Excellency Ato Bezabih Gebreyes, Civil Service Commission Commissioner, and other higher government officials, representatives of the embassies and the University Community.



**Ato Bezabih Gebreyes**
*Civil Service Commission Commissioner*



**Professor Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University President*

Ato Bezabhi, Civil service Commission Commissioner, in the occasion congratulated the graduates, the family of the graduates and the university community and gave working directions to the graduates.

He also mentioned that since its establishment the Ethiopian Civil Service University has been discharging its mission in building the capacity of the public sector through its different specialized programs, short term training, consultancy and research and community service. The University has been instrumental in the implementation of the Civil Service Reform Programmes and played a key role in the development of the civil service and build the capacity of government officials in the country.



*Guest of honors and ECSU senate member*

Ato Bezabhi appreciated the University for providing scholarship for neighboring countries Civil Servants and urged the University to continue its commendable efforts of assisting the neighboring countries in particular and African countries in general in their human development efforts.



*Ato Bezabh, awards Gold medals to distinct graduates.*

Finally he urged for the employees and graduates to participate and support ambition plan to plant seedling launched at the national level and play great role to save the environments.



*Professor Fikre , awards and put on a doctoral hood to PhD students*

In his opening remarks, Ethiopian Civil Service University President, Professor Fikre Dessalegn, congratulated the graduates for their biggest achievements. He said you are climbing new heights of success, you are primary drivers in the economic development of the country .The knowledge, skills and attitudes you have got while staying in our university and in your life time change in to real world and serve the community and their country at large. He also reminded them to be an ambassador for their university by their good service and virtues.





The University has been supporting the government efforts to improve the civil service sector by opening new Programmes, strengthening the training and consultancy services and conducting problem solving researches. Professor Fikre indicated that the University has graduated over 35,000 civil servants that contribute to the development of the country and played a key role in the development of the civil service and in build the capacity of government officials in the country since 1995.



Guest of honor of the ceremony, Ato Bezabh, has handed out awards and degrees for graduates and Gold medals to distinct graduates. The University graduated 1531 students with first, second and third degrees.



In order to be competitive and selective educational institution ECSU is working hard to enhance its internal capacity and modernize itself to meet its mission and able to answer the timely demands of the public services Professor Fikre underscored.





# ECSU Council Evaluates the Annual Plan Performance

Ethiopian Civil Service University council held tow days annual work plan evaluation and approved the next year annual work plan draft from 8 to 9 July 2019 at Hidasse Hall. All ECSU directors, college deans, team leaders and ECSU higher managements have participated on the evaluation.

In his opening speech president of Ethiopian Civil Service University, Professor Fikre Dessalegn, welcomed the participants and said this evaluation is a continuation of the previously conducted three consecutive quarterly work plan evaluation programs. During our deep renewal evaluation we identified our weaknesses and work hard to improve them. Each wing will be evaluated in accordance with its BSC plan action performance of year 2011 E.C. Based on this evaluation results, we deeply evaluate and approve the draft of the 2012E. C annual work plan, he added.



**Professor Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University President*

On the tow days evaluation the university Academic wing, Administrative and Students' Service , Research and Community service, Training and Consultancy wings and Management support wing presented their respective wings annual work plan performance for evaluation. The council raised different questions and held extensive discussions on work performance report presented by each vice president.

Ato Nesru Awel, the university Planning, Monitoring and Evaluation Directorate Director, also



**Ato Nesru Awel**
*Planning, Monitoring and Evaluation Directorate Director*



**Dr. Lemma Gudissa**
*Academic Vice President of ECSU*

presented the next year annual draft work plan prepared by the ECSU Institutional Planning and Assessment Directorate and gave a highlight on what an effective BSC plan contained.

In his closing remark, Professor Fikre said in year 2011E.C our overall performance is at a good level. For the coming academic year, we must strengthen our efforts and work hard standing together to achieve our goal in the next year activity to exceed our expectations in the performance category he underscored. Finally, he thanked the council for the efforts on achieving the annual performance of the university and gave direction for the coming year annual plan implementation.



# ICTD
# GIVES TRAINING

Information Communication Technology Directorate in collaboration with Google gave first round training on digital skill on July 18, 2019 at Development learning Center for ICTD experts and other administrative and academic staffs.





**Ato Yitbarek Ibrahim**
*Director of Information Communication Technology Directorate*

Ato Yitbarek Ibrahim, Director of Information Communication Technology Directorate, said these kinds of training help employee aware on issues of new technologies and create platforms to develop employee skill. Through programs like these, we aim to help employee access the best of Google's training and tools to grow their skills, careers, and businesses.



In addition the directorate has a plan to train the IT experts on different topics to fill their skill gaps in the coming academic year he added.

The training focused on Building Online strategy, Marketing websites, Search Engine Optimization (SEOs), Search Engine Marketing (SEM), AdW0rds and Digital Opportunities.



# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ

## የ2011 ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ግምገማ ቅኝት

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የፐብሊክ ሰርቪሱን አቅም ለመገንባት ተልዕኮ ከተሰጣቸው ተቋማት መካከል አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት በጥናት ላይ የተመሰረቱና አግባብነት ያላቸውን የቅድመና የድህረ-ምረቃ ስፔሻላይዝድ የትምህርት ፕሮግራሞችን ቀርጾ በማስተማር፣ አጫጭርና ተከታታይነት ያላቸውን ስልጠናዎች አዘጋጅቶ በመስጠት የመንግስት ሰራተኞች የአመለካከት፣ የእውቀትና የክህሎት ክፍተቶች እንዲሞሉ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፐብሊክ ሰርቪሱ አደረጃጀት፣ አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ላይ ጥናትና ምርምር በማካሄድ እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት፣ በሀገሪቱ እየተካሄደ ባለው ሪፎርም መሰረት በፐብሊክ ሰርቪስ ተቋማት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ከማስቻል አንጻር ግንባር ቀደም ሚና እየተወጣ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርስቲው ይህንኑ ኃላፊነቱን በተጠናከረ መልኩ ለመወጣት እንዲችል የአምስት ዓመት (2008-2012) ስትራቴጂክ ዕቅድ በመንደፍ እና ከስትራቴጂክ ዕቅዱ በመነሳት ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ሲተገብር ቆይቷል፡፡ በ2011 ዓ.ም በጀት ዓመትም ከስትራቴጂክ ዕቅዱ እና ከ2010 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በመነሳት የዩኒቨርሲቲው የ2011 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ የተገባ ሲሆን አጠቃላይ የ2011 በጀት ዓመት አመታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትም በተቋማዊ ዕቅድ ዳይሬክቶሬት አማካይነት ለዩኒቨርቲቲው ማህበረሰብና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ተደርጓል ፡፡

ከቀረበው ሪፖርት ለመረዳት እንሚቻለው ዪኒቨርሲቲያችን በ2011 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድ ሰፊ ስራዎችን ያከናወነ ሲሆን በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ዕቅዱን በመከለስ በአራቱም ዕይታዎች ለማከናወን ያቀዳቸውን ተግባራት የአፈፃጸም ደረጃቸው ተለክቷል፡፡

በዚህም መሰረት ዩኒቨርሲቲው በ2011 ዓ.ም የተገልጋይና ባለድርሻ አካላት እርካታ ለማሳደግ ባደረገው ጥረት አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በሰጣቸው በመማር ማስተማር፣ ስልጠናና ማማከር፣ ምርምርና ማህበረሰብ እና አስተዳደራዊ ድጋፎች የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ለመለካት ኮሚቴ ተቋቁሞና በመስክ የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ተሰርቶ በ3ቱ ዋና ዘርፎች አማካይ የዕርካታ መጠን 79.2 ከመቶ የደረሰ ሲሆን በአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ዘርፍ እና በማኔጅመንት ድጋፍ አገልግሎቶች እርካታ በቅደም ተከተል 74.85 ከመቶ እና 74.55 ከመቶ መሆኑ ታውቋል :: ይህም በተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ዕይታ የተገኘው ውጤት በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር 98 ከመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡

የዩኒቨርሲቲውን የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ከማሻሻል አንጻር የበጀትና የፋይናንስ አጠቃቀም ለህዝብ ግልጽ ለማድረግ በታቀደው መሰረት የበጀትና የፋይናንስ አጠቃቀም በዩኒቨርሲቲው ድህረ ገጽና በማስታወቂያ ሰሌዳ በመለጠፍ ለህዝብ ግልፅ ተደርጓል፡፡ በውስጥና በውጪ ኦዲተሮች ሪፖርቶች ላይ በመመርኮዝ የእርምት እርምጃዎች መወሰዳቸውን የማረጋገጥ ሥራ ተከናውኗል፡፡ የፋይናንስና ንብረት ኦዲት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲደርስ ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪወርሃዊየጥሬገንዘብቆጠራበተመለከተ4ወራዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በ2011 በጀት ዓመት በIFMIS ላይ ስልጠና እንዲሰጥ በማድረግ የክፍያ ስርዓቱ፣ የንብረት ወጪ እና የንብረት አመዘጋገብ ስርዓት በመዘርጋት፣ የተማሪዎች የገንዘብ አሰባሰብ በIFMIS እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በተሰጠው ጣሪያ መሰረት የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ጥያቄ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በ2011 በጀት ዓመት ያቀዳቸውን ስራዎች ለማከናወን በጠቅላላው ከተፈቀደው በጀት ከብር 508,635,446.14 ውስጥ 459,963,173.13 (90.43%) ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በተሰብሳቢ ሂሣብ ለኮንስትራክሽን የተከፈለ ከወጪ ቀሪ 12,476,958.50 እና ሌሎች በተሰብሳቢ የተያዙ ክፍያዎች ብር 2,512,055.41 በተጨማሪም፣ ሲጨመርበት 474,952,187.04 (93.38%) ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

የንብረት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓትን ለማሻሻልም በIFMIS ስርዓት የንብረት ምዝገባ በማካሄድ በተዘረጋው ስርአት መሰረት ንብረቶች ገቢና ወጪ እየተደረጉ ይገኛል:: የንብረት አያያዝን በ25 በመቶ ኮምፒውተራይዝድ ለማድረግ ታቅዶ ከዕቅድ በላይ 50 ከመቶ የንብረት አያያዝ ኮምፒውተራይዝድ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በጥገና፣ በንብረት አመዘጋገብ፣ አጠቃቀምና አያያዝም ብር

30,046.63 ከብክነት ለማዳን ተችሏል ። ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት እንደማይሰጡ በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የተለዩ ብር 402,000 የሚያወጡ ንብረቶች ለ15 ተቋማት ድጋፍ እንዲደረግላቸው በጠየቁት መሰረትተሰጥቷል። በንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ተለይተው በጨረታ በሽያጭ የተለያዩ ንብረቶች በብር 298,543 እንዲወገዱ ተደርጓል።

በበጀት ዓመቱ የገቢ ምንጮችን ማስፋፋትና ገቢን ማሳደግ በተደረገው ጥረት የውስጥ ገቢ በህግና በሥርዓቱ መሰረት መሠብሠቡን፣ መያዙንና ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በተደረገው ክትትል ከውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 38,980,200 ውስጥ ብር 37,224,470.69 (95.50%) መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ከፕሮጀክት ስምምነቶች ደግሞ ብር 70,000,000.00/ሰባ ሚሊዮን ብር/ ያልተጣራ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 91,731,841.84 (131%) መሰብሰብ ተችሏል።

በፋይናንስ ዕይታ የተቀመጡ የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሻሻልና የገቢ ምንጮችን በማስፋፋት ገቢን ለማሳደግ የሚያስችሉ ግቦች በዕቅድና በበጀት ዝግጅት የአፈጻጸም ግምገማ፣ በንብረት አስተዳደር ስርዓት፣ ከተለያዩ አገልግሎቶች ገቢ ለማሳደግ የሚያስችሉ ዋና ዋና ተግባራት ክንውን ከተቀመጠው ዕቅድ አንጻር ሲነጻጸር ውጤቱ 16.57 ሲሆን አፈፃፀሙም 165.7 ከመቶ ለመሆን ችሏል::

የዩኒቨርሲቲውን አገልግሎቶች አግባብነት፣ ጥራትና ተደራሽነት ማሳደግም የተቋሙ ገጽታ ግንባታ የሚያጠናክሩ ስራዎች ለማከናወን በታቀደው መሰረት አንድ የ30 ደቂቃ ዶክመንተሪ በማዘጋጀት በተለያዩ ፎርማቶች ተሰራጭተዋል፤ ዘጠኝ ወርሀዊ መጽሄቶች እና አንድ የስድስት ወር መጽሄት ተዘጋጅቷል ። በውስጥ አቅም 24 የሁነቶች ቪዲዮዎች ተዘጋጅተው በዩኒቨርሲቲው ዌብሳይት፣ በዩቲዩብ፣ በፌስቡክ፣ ተሠራጭቷል፣ ሃምሳ አንድ የሚሆኑ ዘገባዎችን በመስራት በዌብ ሳይትና በሶሻል ሚዲያ አማካኝነት ተላልፈዋል። የዩኒቨርሲቲው ምሁራን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ላይ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡ በተጨማሪም ተቋሙን የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰሩ ተደርጎአል። ሀገር አቀፍ ወርክ ሾፕ ሙሉ ለሙሉ በተለያዩ ሀገር አቀፍ ሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጎአል። ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ስራዎች ሀገር አቀፍ የከተሞች ፎረም ላይ በመወከል የማስተዋወቅ ስራ የተሰራ ሲሆን አመታዊ የ AIGAD ዎርክ ሾፕ እንዲሁም የሁለት አህጉር አቀፋዊ አጀንዳዎች ገለጻዎች ሙሉ ለሙሉ ተቀርፆ በተለያዩ ሚዲያዎች ተሰራጭተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ልዩ ልዩ መረጃዎችን በዌብ ሳይት፣በዩቱብ፣ በፌስቡክ፣ እና በዩኒቨርሲቲው አውትሉክ ማሰተላለፍ ተችሏል። የሥልጠና፤ የማማከርና የፋሲሊቲ አገልግሎቶችን በተለያዩ ክልሎች የማስተዋወቅ ሥራዎች የተሰራ ሲሆን 5 የተከታታይ ትምህርት አማራጭ መርሀ-ግብሮች ዝርዝር በዩኒቨርሲቲው ድህረ ገጽ በመልቀቅ የማስተዋወቅ ስራ በስፋት ተሰርቷል ። እንዲሁም የትምህርት ዘመኑ ማጠናቀቂያ ምረቃን በቀጥታ ሥርጭት እንዲከናወን መደረጉ ስለዩኒቨርሲቲው እንቅስቃሴ ሁኔታ ሕዝቡ እንዲያውቅ ዕድል ፈጥሯል።

የትምህርት ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ የትምህርት ፕሮግራሞች የካሪኩለም ዝግጅትና ክለሳ የማድረግ ስራን በተመለከተ በመጀመሪያ ድግሪ 8፣ በሁለተኛ ዲግሪ 26 እና በሶስተኛ ዲግሪ 6 ከሪኩለሞች ክለሳ ተደርጎላቸዋል፤ ስምንት አዳዲስ ፕሮግራሞች እየተዘጋጁ ይገኛል። በየኮሌጆቹ ደረጃም አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞች ለመክፈት ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ሌሎች አዳዲስ ፕሮግራሞችን ለመክፈት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ በሥርዓት ትምህርት ኮሚቴ ታይተው በሰኔት እንዲጸድቁ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፈዋል። በመምህራንና በድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የሚሰሩ ምርምሮች ጥራት እንዲኖራቸው በስታቲስቲክስና ኢኮኖሚክስ የማማከር ድጋፍ የሚሰጥ (Statistical Advisory Service) አገልግሎት የተቋቋመ ሲሆን ለዶክትሬት ዲዘርቴሽን ፅሑፍ የቋንቋ አጠቃቀም ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት (Language Proficiency Check Service) ማቋቋሚያ ጥናት ተጠናቆ እጩ የዶክተሬት ተማሪዎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል።

የቤተ-መፅሐፍት አገልግሎትን ለማዘመን የማጣቀሻ መፅሐፍት ሙሉ በሙሉ አውቶሜት እንዲሆኑና አብያተ-መፅሐፍቱም የ24 ሰአት አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ወቅታዊ የሆኑ ፕሬዲካልስ ጽሁፎች፣ ጋዜጣና መጽሄት እንዲቀርቡ፣ ቤተ-መፅሐፍቶቹ የዲጂታል አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ለጥናትና ምርምር የሚጠቅሙ መጻህፍትና የመመረቂያ ጽሁፎችን ዝግጁ ማድረግ ተችሏል። ከዚህም በተጨማ በግሪንስቶን ሶፍትዌር አማካይነት የመጽሐፍቶች (ዳታ) የማስገባት ተግባር በማከናወን 9,589 (e-Books) ከዋናው ሰርቨር ጋር በማገናኘት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ተደርጎአል:: ይህም በገንዘብ ሲተመን 11,102,504.38 ለዩኒቨርሲቲው እሴት ተጨምሮአል። የ4 የሞጁላር ትምህርት ሥርዓትን ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር ለማቀናጀት (Blended-Learning) ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል።

የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የተማሪዎች ቅበላ አቅም በማሳደግ እና የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን በዓይነትም በቁጥርም ማስፋፋት ስራዎች ተሰርተዋል። የትምህርትን ተደራሽነት ለማሻሻል የትምህርት መርሀ ግብሩ በክረምት፣በማታ እና በእረፍት ቀን እንዲስፋፋ ተደርጓል። የአዳዲስ ፕሮግራሞች ቀረፃን በተመለከተ በየኮሌጁ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እየተደረገ ይገኛል።

በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች ጥራትና አግባብነትን ለማስጠበቅ የስልጠና ፕሮግራሞች በጥንድ የማሰልጠን ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ 26 አዳዲስ የስልጠና ማቴሪያሎች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ በማድረግ በስልጠና ስራ ላይ ውለዋል፣ 38 የስልጠና ማቴሪያሎችም ተከልሰዋል። ተቋማት ስልጠና በሚጠይቁበት ጊዜ Mini Need Assesment በማካሄድ ስልጠናዎችን ደንበኛ ተኮር የማድረግ ስራ እየተከናወነ ይገኛል። የስልጠና ሞጁል ዝግጅት ጋይድላይን በመጠቀም የስልጠና ሞጁሎች ደረጃቸውን እንዲጠብቁ

ተደርጓል፤ በተቀመጠዉ መስፈርት መሰረት 18 የስልጠና ሞጅሎች ተዘጋጅተዋል። የስልጠና ጥራት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ 3 ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረው እንዲስፋፉ ተደርጓል።

የጥናትና ምርምር ስራዎች ለማጠናከር የምርምር ንድፎችን በበጀት ለመደገፍ በተቀመጠ ጊዜ ሰሌዳ እንዲጠናቀቁ ማድረግና በጥራት ማስጠበቂያ መንገዶች እንዲያልፉ የማደረግ ሥራ ተሠርቷል:: በበጀት ዓመቱ 27 ምርምሮች ለማጠናቀቅ በተያዘው እቅድ መሰረት 22 የምርምር ንድፎች ተገምግመው የበጀት ድጋፍ አግኝተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል ። የ6 ምርምሮች የመረጃ ማሰባሰብ ስራዎች እየተከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተለያዩ የምርምር ውጤቶችን በሳይንሳዊ ምርምር ጆርናል (African Journal of Leadership and Development) ለማሳተም የኢዲቲንግ ሥራው ተጠናቆ የህትመት ውጤት በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

በየማዕከሉ የተሰሩት ምርምሮች የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ (HERQ) እና የዩንቨርስቲዉን ደረጃ የጠበቁ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩት የምርምር ዉጤቶች አስተችቶት ተካሂዷል። የምርምር ስራዎች ቫሊዴሽን እና ሪቪው ዎርክሾፖችን የማዘጋጀት የማስተቸትና ግብአት የማግኘት ሥራ ተሠርቷል። ዩኒቨርሲቲያችን አዲስ ከተጀመሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ጎን ለጎን ቀድሞ የተጀመሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ተጠናቀው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ለማድረግ ባደረገው የክትትልና ድጋፍ 6 የተጠናቀቁ የምርምር ውጤቶችን በጆርናል የማሳተም ስራ ተከናውኗል፤22 የተጠናቀቁ የምርምር ስራዎችን በፕሮሲዲንግ የማሳተም ስራ ተጠናቋል። ለዓመታዊ ኮንፈረንስ ዝግጅትከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እና ተመራማሪዎች የምርምር ውጤታቸውን እንዲያቀርቡ በተደረገው ጥሪ መሰረት 108 የምርምር ስራዎች ለኮንፍረንስ እንዲሁም 17 የምርምር ስራዎች ለጆርናል ህትመት ተሰብስበዋል።

አስተዳደራዊ ድጋፍ ስራዎችን ለማጠናከር በታቀደው መሰረት የአስተዳደራዊ ድጋፍ ስራዎች የማጠናከር ስራ የተሰራ ሲሆን በዩኒቨርሰሲቲውና በግዢ ኤጀንሲ ድረ ገጽ ለደንበኞች 15 የጨረታ ውጤቶችን ግልፅ ለማድረግ ታቅዶ 14 ለማከናወን ተችሏል። የJEG ድልድል ስራም ተጠናቆ 845 የአስተዳደር ሰራተኞች በድልድሉ ቦታ የተሰጣቸው ሲሆን ከምደባው ሂደት ጋር ተያይዞ የተነሱ ቅሬታዎችንም በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲሁም በየደረጃው ኮሚቴ በማቋቋምና ለማኔጅመንቱ የውሳኔ ሃሳብ እንዲቀርብ በማድረግ የሰራተኞቹ ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ተደርጓል። በድልድሉ ምደባ ላላገኙ 38 ሠራተኞች ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አማራጭ ሀሳብ በማቅረብና በማፀደቅ ምደባቸውን እንዲያገኙ ተደርጓል። ዩኒቨርሲቲውን የሰው ሀይል ለማሟላትም የ74 የአካዳሚክና የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር ሲፈጸም የ9 የአስተዳደር እና የ1 የአካዳሚክ ሠራተኛ ከሌላ መስሪያ ቤት ወደ ዩኒቨርሲቲው ዝውውር ተፈጽሟል:: ለ8 የአካዳሚክ ሰራተኞች የማዕረግ ለውጥ ተደርጓል።

የመማር ማስተማር፣ የስልጠናና ማማከር፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለመደገፍ የህትመትና 20 ሺህ የብዜት ውጤቶችን በስራ ትዕዛዙ መሰረት በሚፈለገው መጠን፤ ጥራትና ጊዜ ለመስራት በታቀደው መሰረት 142 ሺህ የብዜት ውጤቶችን ለመስራት ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ መልካም ሥነ-ምግባር ሊያጎለብቱ እንዲሁም ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ 2345 የህትመት ውጤቶች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተሰራጭቷል። የመማር ማስተማሩን ዘርፍ በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ኢንትሮዳክሽን ቱ ፐብሊክ ፖሊሲ 6 ምዕራፎች ያሉት በቪዲዮ ብለንድድ ኮርስ ቀረጻ ተደርጓል፣ ለ303 ተማሪዎች በኢለርኒግ ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል።

የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለማጠናከር የማህበረሰብ አገልግሎቶች ፍላጎትን በተመለከተ ከውስጥና ከውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከርና የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የመለየት ሥራ በዕቅዱ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሰርቷል። በሶስት የመንግስት ት/ቤቶች ዘመናዊ የቤተ-መጻሕፍት አደረጃጀትና የኮምፒዩተር አጠቃቀምን ያካተተ ተከታታይ ሥልጠና ፕሮግራም ተግባራዊ ተደርጓል። በማህበረሰብ ራዲዮ በተለያዩ ፕሮግራሞች ለ1825 ሰዓት ለማስተላለፍ ታቅዶ 1822 ሰዓት የሸፈኑ ፕሮግራሞች ማስተላለፍ ተችሏል። 27 የማህበረሰብ አገልግሎት የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ለመስጠት ታቅዶ 24ቱን መስጠት ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 እና በሌ ክ/ከ ወረዳ 9 አስተዳደር ፅ/ቤት ለተወጣጡ ሰልጣኞች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል። በዚህም ብር 48,818.88 የሚጠይቅ ስልጠናን በማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል። በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ውስጥ የሚኖሩ ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ ህጻናትን ያሉበትን ሁኔታ በማጥናትና ችግሮች በመለየት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በማስተባበር 4 ማዳበሪያ አልባሳት እና 9,735 ተሰበስቦ ለሚመለከታቸው ገቢ ተደርጓል።

የፐብሊክ ሰርቪሱ የሰው ሀይል የሚያጎለብቱ ስራዎች ከማሳደግ አንጻር የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን ከመስጠት አኳያ በበጀት ዓመቱ የአዳዲስና ነባር ተማሪዎች በአጠቃላይ 6824 (ወ=5195፣ ሴ=1629) ተማሪዎች ተመዝግበው የመማር ማስተማር ሥራው በተገቢው ሁኔታ ተሰጥቷል። በፕሮጀክት ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር 15 ተማሪዎችን፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ 105፣ ከብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት ቢሮ በአመራር 12 ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተና አልፈው ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ተደርጓል። ከጎረት ሀገሮች 94 ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛል። በበጀት ዓመቱም በፒ.ኤችዲ 29 (27 ወንድ እና 2 ሴት)፣ በማስተርስ ዲግሪ 1,398 እና በመጀመሪያ ዲግሪ 108 በድምሩ 1,531 (1,111 ወንድ እና 420 ሴት) ተማሪዎች ትምህርታቸው አጠናቅቀው ተመርቀዋል:: ለተለያዩ

ተቋማት የሚሰጠው የሠራተኛ ቅጥር እና የደረጃ እድገት የፅሁፍ ፈተና አገልግሎትን ደረጃውንና ምስጢራዊነቱን በጠበቀ መልኩ እየተሰጠ ይገኛል። በመሆኑም ከ42 የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ለቀረቡ የሰራተኛ ቅጥርና የደረጃ እድገት የጽሁፍ ፈተና አገልግሎት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ተሰጥቷል።

የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በተመለከተም ለፐብሊክ ተቋማት አጫጭር ስልጠዎችን በመስጠት የሰው ሀይል የመፈጸም አቅምን ለማሻሻል የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራት በታቀደው መሰረት ለ64 ተቋማት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ82 ተቋማት የስልጠና አገልግሎት ሲሰጥ ለ7,000 ሰልጣኞች የስልጠና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ9,024 ሰልጣኞች አገልግሎቱ ለመስጠት ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር ከጉምሩክ ስርአት ጋር በተያያዙ 14 የስልጠና ርእሶች ተለይተው የስልጠና ሞጁል ለማዘጋጀት የስራ ውል ሰነድ በመፈራረም የስልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅተዋል።

የፐብሊክ ተቋማትን አሰራርና አደረጃጀት ማማሻልን በተመለከተም ለ10 ደንበኛ ተቋማት የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ8 ደንበኛ ተቋማት አገልግሎቱ ተሰጥቷል። ከዚህም በተጨማሪ የማማከር አገልግሎቶች ያገኙ ተቋማት ላይ የድህረ ማማከር ክትትልና ድጋፍ በ6 ተቋማት ላይ የተሰራ ሲሆን አንድ የተቋማዊ መዋቅር ማሻሻያና የስራ ዝርዝር ጥናት የማማከር ስራ በመስራት ላይ ይገኛል። የምክክር መድረክና የማማከር አገልግሎት ስራዎች ላይ በሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ጉዳዩች ወርክሾፖችን ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት አንድ ሀገራዊ የምክክር መድረክ ተከናውኗል።

የከተሞች የመዋቅራዊ ፕላን ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት የጋምቤላ እና የአሶሳ ማስተር ፕላን ሲጠናቀቅ የኮምቦልቻ መዋቅራዊ ፕላን በከተማ አስተዳደሩ እንደገና ፕሮጀክቱ እንዲጀመር በቀረበው ጥያቄ መሰረት ስራው እየተሰራ ይገኛል። የአዲስ አበባ መዋቅራዊ ፕላን አተገባባር የስልጠና ፕሮጀክት በውሉ መሰረት እየተሰራ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ ለአካባቢ፤ የደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን አንድ የተቋማዊ መዋቅር ማሻሻያና የስራ ዝርዝር ጥናት የማማከር ስራ ተሰርቷል። በራስ ተነሳሽነት የማማከር ሥራን በመቅረፅ ገቢን ለማሳደግ በተያዘው እቅድ መሰረት አንድ የስርዓተ ፆታ ማካተቻ ማኑዋል ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ተሰርቷል።

የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ከማሳደግ አንጻር የሴቶችና ሌሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካላት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ታቅዶ በተማሪዎች መረጣ ለሴት ተማሪዎች አዎንታዊ ተሳትፎ አመራረጥ እና የሴት ተማሪዎች ቅበላ እንዲጨምር ተደርጓል:: ለሴትና ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የድጋፍ አገልግሎታችን ለመስጠት ፍላጎትን የመለየት ስራ ተሰርተቶ ድጋፍ ተደርጓል። ከተለያየ ክልል ህጻን ልጅ እና ሞግዚት ይዘው ለመጡ ሴት ሰልጣኞች ስልጠናቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ የማድረገ ስራ ተሰርቷል። የስርዓተ- ጾታ አካታችነትን ለመከታተል በሥልጠና ማቴሪያል መመሪያ እንዲካተት ተደርጎል፤ ከዚህም በተጨማሪ ከቤተሰብ መምሪያ ጋር ትስስር በመፍጠር ለ40 ሴት ሠራተኞች የማህጸንበርካንሰርየምርመራእናየህክምናአገልግሎትበነጻ እንዲያገኙ ተደርጓል። በሁሉም ግቢዎች ለአካል ጉዳተኞች መግቢያና መዉጫዎች የሚሆኑ መንገዶች ተሰርተዋል፤ ከዚህም በተጨማሪ በመደበኛነት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ብር 92,550 ክፍያ ተፈጽሟል፤ ባጋጠማቸው የአካዳሚክና የማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በጠቅላላው ለ28 ሠራተኞችና ተማሪዎች የምክር አገልግሎቱ እንዲያገኙ ተደርጓል። ለ158 ሴት ተማሪዎች የሳይኮሶሻል የምክር እና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን የተሰጠ ሲሆን ለ822 ሴትና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል። በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና በሥራቸው ባህሪ ምክንያት ተጋላጭ በሆኑ የዩኒቨርሲቲያችን ሠራተኞች ዙሪያ የኤችአይቪ/ኤድስ የተጋላጭነት የዳሰሳ ጥናት (Mini Assessment) ተካሂዷል። በዚህም ለሚቀጥለው በጀት አመት ጠቃሚ የሆኑ አመላካች ግብዓቶች ተገኝተዋል። ኤች.አይቪ/ኤድስ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫና የህይወት ክህሎት ስልጠና ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተሰጠ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ሬዲዮ በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ተሰርቷል።

በውስጥ አሰራር ዕይታ ስር የተቀመጡ ሶስት ግቦች የዩኒቨርሲቲውን አገልግሎቶች አግባብነት፣ ጥራትና ተደራሽነትለማሳደግ፣የፐብሊክሰርቪስየሰውሀይል፣አሰራር አና አደረጃጀት የሚያጎለብቱ አገልግሎቶችን ለማሳደግ እና የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሳደግ ፤ ተቋማዊ ገጽታ ግንባታን፣ አስተዳደራዊ ድጋፍ ስራዎችንና የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለማጠናከር፤ የረጅም እና የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የሴቶችና ሌሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካላት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና በኤች.አይቪ/ኤድስ ግንዛቤ ማስጨበጥና ለውስጥ አሰራር ከተቀመጠው የአፈጻጸም መለኪያ ክብደት 40 ከመቶ አንፃር የአፈፃፀሙ ውጤቱ 48 ከመቶ ሲሆን ይህም ከዕቅድ አንፃር ሲነጻጸር 120 ከመቶ ማከናወን ተችሏል::

የመማማርና ዕድገት ዕይታ አንጻር በበጀት አመቱ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት መካከልም የሰው ሀይል ብቃትና ተወዳዳሪነት ለማሻሻል ዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የተጣለባቸውን ሀላፊነት በአግባቡና በተገቢው መንገድ መወጣት እንዲችሉ በረጅም ጊዜና አጭር ጊዜ ስልጠና ሰራተኞች አቅማቸውን እንዲገበነቡ ያደርጋል። በዚህም መሰራት የረጅም ጊዜ ስልጠና በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በመጀመሪያ ፣ በሁለተኛና በሶስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ የተደረገ ሲሆን በአጠቃላይ 90 የአካዳሚክ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛል::

ከዚህም ባሻገር ለአካዳሚክ እና የአስተዳደር ሰራተኞች በተለያዩ ርዕሶች የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን የሶስተኛ ዙር የHDP ስልጠና ለ32 መምህራን እየተሰጠ

ይገኛል። ለ28 የስርዓተ-ትምህርት ክለሳ ቡድን አባላት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የህይወት ክህሎት ፣ በGIS ፣ Blended Digital Training Materials Design and Development ስልጠና ፣ በካይዘን ትግበራ ፣ በውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም አዘገጃጀትና የፕሮግራም በጀት ጥያቄ አቀራረብ ፣ ከሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ጋር የተገናኘ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል። Human Capital Development ሥልጠና ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሠረት ዳይሬክተሮቹ፣ ዘርፍ ኃላፊዎች፣ ቡድን መሪዎች እና ኤክስፐርቶች ሥልጠና ተሰጥቷል፣ ከዚህም በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው አዘጋጅነት ለ971 የአካዳሚክና የአስተዳደር ሰራተኞ በተለያዩ እርሶች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል።

መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲን ለማስፋፋትና ለማዘመን በታቀደው መሰረት የግዢ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ቋሚ ዕቃዎች፣ የጽዳት፣ የጽህፈት መሳሪያዎች፣የቴክኒክ ዕቃዎች፣ የደንብ ልብሶች፣ ለመማር ማስተማር የሚሆኑ መጽሀፍቶች እና ኦርጅናል የትምህርት ማስረጃ ሰርተፍኬት ግዢ ብር 26,290,513.27 ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። በወሊሶና በአዲስ አበባ ለሚገነቡ የካፒታል ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 230.1 ሚሊዮን ተመድቦ ስራዎች በተቀመጠላቸው ፕሮግራም መሰረት እየተሰሩና የጊዜ ሰሌዳም በማስቀመጥ ከፍተኛ አመራሩ እና ፕሮጀክቱን የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች ጋር ውይይት በማድረግ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም እየተገመገመ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲው ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገራት ጋር ያለውን አጋርነት የሚያጠናክሩ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ሲሆን ከጎረቤት ለ82 ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ለመስጠት ታቅዶ 94 ተማሪዎች የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከውጭ ሀገር የሚመጡ ተማሪዎችን አስመልክቶ ከየአገራቱና ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በጋራ የመስራት ልምድ ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል። ከጀርመኑ Khle ዩኒቨርሲቲ እና ከደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ ጋር በጥምራ በBlended Learning ፕሮግራም በማስተርስ ፕሮግራም በህዝብ አስተዳደር እና በዓለም አቀፍ ልማት ትብበር በ2012 በጀት ዓመት ትምህርቶችን ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል:: ከዚህም በተጨማሪ ከሁዋዌ (Huawei) እና ከሲስኮ (Cisco) ካምፓኒዎች ጋር በጋራ ለመስራት የመጀመሪያ ደረጃ ግንኙነት ተደርጓል። በአቅም ግንባታ ዙሪያ ከተባበሩት መንግስታት ሀቢብታት እና IHS-Erasmus University ጋር በመሆን የከተማ አቅም ግንባታ ለመሥራት በመስማማታቸው የመግባቢያ ውይይት ተደርጓል።

ከዚህ ባሻገር ዩኒቨርሲቲው በሀገር ውስጥ ካሉ አጋሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችሉ ስራዎች በዕቅድ መሰረት እየተሰሩ ሲሆን ከ4 አጋር ተቋማት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ታቅዶ ከ7 አጋሮች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ተችሏል። በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲያችን ከሀገር ካሉ አጋሮች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶች በመፈራረም በትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከርና በምርምር ላይ ሰፊ ስራዎችን እየሰራ የሚገኝና ከውጪ አጋሮችም ጋር ያለው ግንኙነት ቀጣይነት እንዲኖረው በተጠናከረ ሁኔታ እየሰራ መሆኑ በሪፖርቱ ተመላክቷል ።

በመማማርና ዕድገት ዕይታ ስር የተቀመጡ ሶስት ግቦች ለማሳካት የሰው ሀይል ብቃትና ተወዳዳሪነት ለማሻሻል፣ መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲን ለማስፋፋትና ለማዘመን እና ከአጋሮች ጋር ግንኙነትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን በአስራ አንድ ወር የአፈጻጸም መለኪያ ክብደት 20 ከመቶ አንጻር የአፈፀም ውጤቱ 17.1 ከመቶ ሲሆን ይህም ከዕቅድ አንጻር ሲነጻጸር 85.4 ከመቶ ማከናወን ተችሏል::

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በአራቱም ዕይታዎች ለማከናወን ያቀዳቸው ተግበራት ከዕቅድ አንጻር አፈፃጸሙ ሲነጻጸር 111.1 ከመቶ ማከናወን መቻሉ በሪፖርቱ ተገልጿል::

ሪፖርቱ ከዚህ በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ የስራ ክንውን የታዩ ደካማ ጎኖች ሲጠቅስ የትምህርት ክፍሎች በSIMS አሠራር ላይ የሚያደርጉት ክትትል አናሳ በመሆኑ ምክንያት ከSIMS የሚገኙት መረጃዎችና ሪፖርቶች አስተማማኝነት ጥርጣሬ ዉስጥ የሚከቱ ሆነዉ መገኘታቸዉ፤ ከአብዛኛዎቹ የሥራ ክፍሎች የሚቀርቡ ሪፖርቶች መዘግየት፣ በአንዳንድ ክፍት የኃላፊነት የሥራ መደቦች ላይ ተወዳዳሪዎች አለማግኘትና ከኃላፊነት የመሸሽ አዝማሚያዎች እየበዙ መምጣታቸዉ፣ በዉስጥ በጀት በሚሠሩ ጥናትና ምርምሮች ላይ የመሳተፍ ዝንባሌ መቀነስ፤ ከዕቅድ ውጭ የሚመጡ ደራሽ ስራዎች ላይ ብቻ በማተኮር በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን በወቅቱ መፈፀም አለመቻል፤ በውል የሚተዳደሩ ግዥዎች የውል ግዜያቸውን በባለሙያ ባለመደገፉ የሚታይ ክፍተት እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን በደካማ ጎን የሚጠቀሱ መሆናቸው ተመላክቷል።

# ለኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ ፖሊሶች ስልጠና ተሰጠ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ለአስራ ስድስት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ካንፓስ ፖሊስ አባላት እና የሽፍት መሪዎች የተቋማት ጥበቃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት ስልጠናውን ያጠናቀቁትን አባላት በ25/10/2011ዓ.ም አስመርቋል፡፡ በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይም ሰልጣኞች በነበራቸው የአንድ ሳምንት ቆይታም በፍጹም ጨዋነትና ጥረት የተሰጣቸውን ሁሉንም የትምህርት ዘርፍ በብቃት ማጠናቀቃቸውን የሚገልጽ የስልጠና ሰርተፊኬት ተሰጥቷቸዋል፡፡









ስልጠናው ሞጁላር የስልጠና ዘዴን የተከተለ ሲሆን የተመረቁት ሰልጣኞችም የወንጀል መከላከል ምንነት በተመለከተ የጥበቃ ስራ ምንነትና አሰፍላጊነት፣ የጥበቃ ዓይነቶች፣ የጥበቃ ዘዴዎችና የተቋም ጥበቃ አለባበስ ስልጠናን ለ6ሰዓት፤ የጥበቃ ስራ ስነ ምግባር፣ የደንበኞች አቀባበልና አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠናን ለ3 ሰዓት፤ የወንጀል ህግ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናን ለ3 ሰዓት፤ ስለግጭት አፈታትና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት ለ3ሰዓት፤ በጥበቃ ስራ የመረጃ አስፈላጊነት፣ ክትትልና ሪፖርት አዘገጃጀት ለ6 ሰዓት የተቋማት ደህንነት ጥበቃ፣ የፍተሻ ዘዴዎች፣ የወንጀል ስፍራ አጠባበቅና እርምጃ አወሳሰድ ስልጠናን ለ6 ሰዓት እንዲሁም የጦር መሳሪያ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠናን ለ6 ሰዓት በድምሩ ለ33 ሰዓታት የሚሰጠውን የትምህርትና ስልጠና መርሀ ግብር በተገቢው ሁኔታ ያጠናቀቁ ሰልጣኞች መሆናቸው ታውቋል፡፡

ስልጠናው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ለአራተኛ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን ከተመራቂ ካምፓስ ፖሊስ አባላትም መካከልም ሁለቱ ሴት ካምፓስ ፖሊስ አባላትም ናቸው፡፡

# የተማሪዎችን ምረቃ በዓል














ECSU

Est. 1995

## International and Public Relations Coordination Directorate

**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.Iprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University

ተገልጋይ ተኮር

ሁሌም መማር

Customer Focus

ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

Continuous Learning

ቁርጠኝነት

Ethiopian Civil Service University

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

Commitment

አሳታፊነት

Collaboration

BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995

**PRINTED BY** *International & Public Relations Directorate*